# <u>የፌዴራል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት የተለያዩ የቅድመ ሥራ ሰልጣኞች የኪስ ገንዘብ አከፋፈል እና ጥቅማጥቅም አሰጣጥ መመሪያ አጭር ማብራሪያ</u>

## 1/ <u>መግቢያ</u>

የፌደራል የፍትህና የሕግ ኢንስቲትዩት በአዋጅ ቁጥር 1071/2010 እንዲቋቋም ሲደረግ ከዚህ በፊት በተለያዩ ተቋማት በተበታተነ ሁኔታ ይሰሩ የነበሩ የሕግ ጥናትና፣ የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ሥልጠና፣ የፍትህ ሥርዓት እና የህግ ትምህርት ማሻሻያ ተግባራትን በማጠቃለል በአንድ ተቋም እንዲከናወኑ ማድረግ በተቋማቱ መካከል ያለውን የኃላፊነት ድግግሞሽ ማስቀረት ሥራውን ውጤታማ ለማድረግ እንደሚረዳ በመገንዘብ እንደሆነ ይታሰባል፡፡

ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲችል በአዲስ ስያሜ አዲስ አደረጃጀት በማዘጋጀት በመንግስት እንዲጸድቅ ለማድረግ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ ኢንስቲትዩቱን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሠማሩ ባለሙያዎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን እና የሌሎች መሰል የምርምር ተቋማትን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በመንግስት ሰራተኞች ሕግና አሰራር መሰረት እንደሚቀጥርና እንደሚያስተዳድር የተመለከተ ቢሆንም ከዚህ በተፈቀደው አደረጃጀት ጉድለት ያለበት በመሆኑ ለአማካሪ ምክር ቤት አቅርበን ችግሩን በመረዳት አቅጣጫ መሰጠቱ አንድ እርምጃ ወደፊት እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ ነባሩን መዋቅር ጠበብ በማድረግ የተሻለ አቅም ያላቸውን ባለሙዎች ለመሳብ የሚያስችል የደመወዝ ስኬልና ጥቅማጥቅም መነሻ ጥናት ፕሮፖዛል ለመንግስት በቅርብ ጊዜ ውስጥ በማቅረብ ይሁንታ ለማግኘት እንደምንችል ሙሉ እምነት አለን፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የፌዴራል የፍትህና የሕግ ኢንስቲትዩቱ በዚህ በጀት ዓመት የሥልጠና ማዕከል ከሌላቸው ስድስት ክልሎች በቁጥር ውስን የሆኑ ቅድመ-ሥራ ሠልጣኞችን በመቀበል ለዳኝነትና ለዐቃቤ ሕግነት እንድያበቃቸው ስልጠና ይሰጣል፡፡ ለሰልጣኞች ወቅቱን ያገናዘበ የኪስ ገንዘብ አከፋፈልና የጥቅማጥቅም አሰጣጥ ሥርዓት ያልተበጀ በመሆኑ በሥራ ሂደት ትልቅ እንቅፋት ሆኖ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በሥራ ላይ የነበረውን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2/ <u>የኢንስቲትዩቱ ዓላማ</u>

በአዋጁ መሠረት ኢንስቲትዩቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1/ ጥናት እና ምርምሮችን፡-

ሀ) የአገሪቱን ህጎች የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስትን በተሟላ ሁኔታ ስራ ላይ ለማዋል፣ የፍትህ እና የሕግ ሥርዓቱን ብቁና ዘመናዊ ለማድረግ፣ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ

እና በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና የእድገት አቅጣጫ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ልማትን ለማፋጠን በሚያስችሉበት ሁኔታ ለማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ ሕጎችን ለማውጣት፣ እና

ለ) የፍትህ አካላትን ዘመናዊ፣ ተደራሽ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ በፍትህ ሥርዓቱ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣

እንዲረዳ ማካሄድ፡፡

2/ የአገሪቱን የፍትህ ሥርዓት ትክክለኛና የተሟላ ገጽታ የሚያሳይ መረጃ እንዲኖር ማድረግ፣ የፍትህ እና የሕግ መረጃ ማዕከል መሆን፣

3/ የፍትህ አካላት አመራሮችን እና ባለሞያዎችን በዕውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከት እና በሥነ-ምግባር በማነጽ የፍትህ ሥርዓቱ ከፍተኛ ሙያዊ ብቃት እና ሥነ-ምግባር እንዲሁም ሕዝባዊ አመኔታና ተቆርቋሪነት ባላቸው እና ለሕግ በላይነት መከበር በጽናት በሚቆሙ ባለሙያዎች የተገነባ እንዲሆን ማስቻል፣

4/ የፍትህ ሥርዓት እና የሕግ ትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራሞችን እና ሌሎች በፍትህ ዘርፉ ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን በማቀናጀት እና በማስተባበር ውጤታማነታቸውን ማረጋገጥ::

ናቸው፡፡

3/ <u>የክፍያ ሁኔታ</u>

የቅድመ ሥራ ሰልጣኞች በሥልጠና ወቅት የኪስ ወጪያቸው እንዲሸፈን የክፍያ ሥርዓቱ ጊዜ ያለፈበት ከ15 ኣመት በፊት ማለትም በ1998 ዓ.ም ይከፈል የነበረው በመሆኑ መሻሻል አለበት፡፡ ከዚህ በፊት ኢንስቲትዩቱ ለቅድመ ሥራ ሰልጣኞች የሚከፈለው የኪስ ገንዘብ ክፍያ በጣም አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ ሰልጣኞች በስልጠና ወቅት ሊቸገሩ የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የክፍያ መጠኑ ማነሱ ምክንያት ስልጠናን በአግባቡ ባለመከታተል ለችግር የሚጋለጡበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡

የሚፈቀደው ክፍያም ቢሆን በጥብቅ ዲስፒሊን መፈጸም እንዲችል ሥርዓት ተበጅቶለታል፡፡ ከዚህ በፊት ከታየው ልምድ በመነሳት ሰልጣኞች ከአቅራቢያው ነዋሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ብድር በመውሰድ ሳይከፍሉ በመቅረት የተለያዩ አቤቱታዎች ለኢንስቲትዩቱ የሚቀርብበት ሁኔታ ነበር፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ታሳቢ በማድረግ ማንኛውም ሰልጣኝ የኪስ ገንዘብ ሲሰጠኝ እከፍላለሁ በማለት ከኢንስቲትዩቱ ቅድሚያ ክፍያ ወይም ብድር እንዳይጠይቅ፣ የኪስ ገንዘብ ሲሰጠኝ እከፍላለሁ በማለት የሥልጠና ማዕከሉ በሚገኝበት አቅራቢያ ከሚገኙ ሱቆች፣ የምግብ ቤቶች፣ ወይም ተመሳሳይ አገልግሎት ከሚያቀርቡ ድርጅቶች ወይም ሰዎች ብድር እንዳይወስድ ክልከላ የተደረገ ሲሆን መውሰድ የተከለከለ ሲሆን ይህንን በመተላለፍ ብድር የተወሰደ ስለመሆኑ

ጥቆማ/አቤቱታ ሲቀርብ ወይም ከአበዳሪዎች ቅሬታ የቀረበ እንደሆነ በዲስፒሊን ግድፈት ተይዞ ለላኪው የፍትህ ተቋም ሪፖርት እንደሚደረግ ተመልክቷል፡፡
የክፍያ መጠኑን ለመወሰን የፍትህ አካላት ስልጠና ማዕከል ባላቸው ሦስቱም ክልሎች የቅድመ ሥራ ሰልጣኞች የሚከፈላቸው የክፍያ ልምድ ዳሰሳ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

**<u>የአማራ ብሔራዊ ክልል ልምድ</u>**

| | የኪስ ገንዘብ | ትራንስፖርት | አበል | ቤት ኪራይ |
|---|---|---|---|---|
| | የቀድሞ ነባሩ ብር 4,809 | ለልምምድ ሲወጡ ይከፈላል | ለልምምድ ሲወጡ ይከፈላል | ለልምምድ ሲወጡ ይከፈላል |
| | አዲስ የተሻሻለው 10,000 ተደርጎ ለክልሉ መንግስት ውሳኔ ቀርቧል | | | |

**<u>የደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ልምድ</u>**

| | የኪስ ገንዘብ | ትራንስፖርት | አበል | ቤት ኪራይ |
|---|---|---|---|---|
| | የቀድሞ ነባሩ ብር 5,081<br>አዲስ የተሻሻለ የለም | ለልምምድ ሲወጡ ይከፈላል | ለልምምድ ሲወጡ ይከፈላል | ለልምምድ ሲወጡ ይከፈላል |

**<u>የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ልምድ</u>**

| | የኪስ ገንዘብ | ትራንስፖርት | አበል | ቤት ኪራይ |
|---|---|---|---|---|
| | -የቀድሞ ነባሩ ብር 5,006<br>-አዲስ የተሻሻለው ብር 7,805 ተደርጓል | ለልምምድ ሲወጡ ይከፈላል | ለልምምድ ሲወጡ ይከፈላል | ለልምምድ ሲወጡ ይከፈላል |

በመሆኑም በዚህ ረቂቅ መመሪያ የክፍያ መጠኑን መካከለኛ ለማድረግ የግምቱን መነሻ ያደረግነው ግብር ተከፍሎ የሚተርፈውን የተጣራ ክፍያ መጠን ከክልሎች የክፍያ መጠን ጋር በማገናዘብ ሲሆን በመጠን ደረጃ ሲታይ አሁንም ቢሆን አነስተኛ ጭማሪ ተደርጓል፡፡

ሌላው ኢንስቲትዩቱ ከክልል ለሚመጡት ማደሪያ አልጋ፣ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስ እና አንሶላ የሚሰጥ በመሆኑ የቤት ኪራይ እንደማይቸገሩ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ የቅድመ ሥራ ሰልጣኙ የተመለመለበት መስሪያ ቤት ደሞዝና ጥቅማ ጥቅም የሚከፍለው ከሆነ ግን ማደሪያ አልጋ፣ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስ እና አንሶላ እንዲሁም ከኢንስቲትዩቱ የሚከፍል የኪስ ገንዘብ ወይም

ሌላ ጥቅማ ጥቅም አይኖርም ማለት ነው፡፡ በዚህ መሠረት የፌዴራል ፍትህና ሕግ ኢንስቲትዩት፡-

<u>**የቅድመ ሥራ ሰልጣኞች የኪስ ገንዘብ አከፋፈል እና ጥቅማጥቅም**</u>

| | የኪስ ገንዘብ | ትራንስፖርት | አበል | ሶፍት | ሳሙና | ሞዴስ | ሜጀሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የቀድሞ ነባሩ ብር 600 (በ1998 ዓ.ም)<br>አዲስ የተሻሻለ 8,000 | ለልምምድ ሲወጡ ይከፈላል | ለልምምድ ሲወጡ ይከፈላል | በወር አንድ | በወር ሁለት ልበስ ሳሙና አንድ የገላ ሳሙና | አንድ ፓኬት ለሴት ሰልጣኝ | አልጋ ከፍራሽ፣ አንሶላና ብርድልብስ ይሰጣል |
| | | | | | | | |

በልምድ ከታዩት ውስጥ ሶስቱም ክልሎች ሳሙና፣ ሶፍት እና የሴቶች የንጽህና መጠበቂያ መሳሰሉትን በጥቅማጥቀም መልኩ አያቀርቡም፡፡

## 4/ ማጠቃለያ

የኢንስቲትዩቱን ከዋና ዋና ተልዕኮዎች አንዱ ሆነውን የቅድመ ሥራ ሰልጣኞችን ማሰልጠን እንዲያስችለው ተመጣጣኝ የሆነ የኪስ ገንዘብ ክፍያ እና ጥቅማ ጥቀም አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡ በሥራ ላይ ላይ የነበረው የቅድመ ስራ ሰልጣኝ ኪስ ገንዘብ አከፋፈል ሥርዓት እና ጥቅማ ጥቅም አሰጣጥ ሥርዓት ጊዜ ያለፈበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1071/2010 አንቀጽ 16(2) ለኢንስቲትዩቱ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የክፍያና ጥቅማ ጥቅም መጠን እንዲሁም የአከፋፈል ሥርዓትን ያካተተው ይህ መመሪያ የክልሎችን ተሞክሮ ባገናዘበ መልኩ ተዘጋጅቶ በፍትህ ሚኒስቴር በኩል አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ ከፍትህ ሚኒስቴር የተሰጡ አስተያየቶች የተካተቱ ሲሆን የሥልጠና ኢንስቲትዩቱ ከሚገኝበት አካባቢ ነዋሪዎች ብድር መውሰድ እና ቅድመ ክፍያ መጠየቅ የመሳሰሉ ጉዳዮች ከመመሪያ እንዲሰረዙ የተሰጠው አስተያየት ባለበት እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በመሆኑም መመሪያው ተመዝግቦና ቁጥር ተሰጥቶ ሥራ ላይ ማዋል እንድንችል እንዲደረግ ከዚህ አጭር ማብራሪያ ጋር ተልኳል፡፡